# እቺን ለኛ ጥሬን ለጌኛ

በልጂግ አሊ

የእግር ኳስ ፌደሬሽን ሚድሮክን ይቅርታ ጠየቀ በሚል በሪፖርተር ድህረ ገፅ ላይ የሰፈረውን ተመልክቼ ሳበቃ በደንብ ከሳቅሁ በኋላ አገራችን የደረሰችበትን ይሉኝታ የሌለበት ስርዓት ሳስበውና ስለስደነቀኝ ለናንተ ይህንን ለመፃፍ ተነሳሁ ።

ጉዳዩ ፌደረሽኑ ከበርቴ አላሙዲንን አለመሸለሙ ሲሆን። የሚደንቀው ግን ሚድሮክ ኢትዮጵያ እየተባለ የሚጠራው የአላሙዲን ድርጅት ባለስልጣን የሆኑት ደክትር አረጋ ይርዳው አለቃቸው አላሙዲን ባለመሸለማቸው ምክንያት ለፌደረሽኑ በፃፉት ደብዳቤ ቅሬታቸውን ስለገለፁና ምንአልባትም ይህ ካልሆን ውርድ ከኔ ብለው ስላስፈራሩ ዶክተር አሸብር የፌደረሽኑ ፕሬዘዳንት በፌደረሽኑ ስም አይገቡ ገብተው ምክንያት ፈልገው ይቅርታ ጠይቀዋል። እኔ በበኩሌ ሌላ የምለው የለም ወደሽ ነው ገጣቢት ንጉስ ትመርቂ ነው።

ፌደረሽኑ የሰጠው ምክንያት አዛውንቱን አላሙዲንን ያታልል እንደሆን እንጂ ማንም ንፁህ አስተሳሰብ ያለውን ግለሰብ አያሳምንም። ምክንያቱን ዶክትር አሸብር በፃፉት ደብዳቤ ባለፈው የሽልማት ስነስርዓት አሰጣጥ ወቅት ሼክ አላሙዲን ያልተዘከሩበት ወይም ያልተሸለሙበት ለተግባራቸው በተመጣጠን ደረጃ በተለየ ስነ ሰርዓት ለመሸለም ታስቦ መሆኑን ያትታል ይላል ሪፖርተር።ይቀጥልና ወደ ፊት ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ በተገኙበት ለአዛውንቱ አላሙዲን በልዩ ስነስርአት ሽልማት እንዲሰጥ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ያረጋግጣል ይላል።

ይህ አደለም የሚያስቀው አዛውንቱ አላሙዲን መሸለም ያልቻሉት ሽልማቱ በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ እንዲሰጥዋቸው ስለተፈለገና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያን ዕለት የአፍሪካ እግር ኳስ ፌደሬሽን ተሸላሚ ስለሆኑ ተሸላሚውን ሸላሚ ማድረግ ስላልተፈለገ ነው ይላል ደብዳቤው።

የሚያስቀው ደግሞ ለሽልማቱ የጠቆማቸውን ግለስብ ስም ዶክተር አሸብርና አቶ አርአያ ተስፋዬ መሆናቸውን ይገልፃል ።ስለጠቆአሚዎቹ ብዙ ማተትም አያስፈልግም።ስማቸው ለምን እንደተጠቀሰ በግልፅ የአራዳ ሚስጥር ነው። ለወዳጆቻቸው እጃቸው እርጥብ ነው የሚባለው አላሙዲን ይህን ስም ሳያዩት እንደማያልፉ እርገጠኛ ነኝ። ካለፉት ግን የሚያናድድ ነው።

ወደ ሽልማቱ ስመጣ ግን ጠቅላይ ሚኒስተሩ በተሸለሙበት ቦታ እሳቸውን መሸለም ተመጣጣኝና በቂ አይደለም ማለት ነው? ይህንን ማንም የሚያምን የለም።ሽልማቱም ተረስቶም የቀረ አይመስለኝም። እንደተለመደው ጠቅላይ ሚኒስተሩ ንብ አልብሰው ከከረሙ በኃላ እንደሸንኮራ መጥጠው እንደ ተጠጣ የኮካ ኮላ ጣሳ ተጠቅመው ከበርቴው በህዝብ እንደተጠሉ ስለሚታወቅ ከከበርቴው ጋር አብሮ መሸለም ውርደትና ጥቅም እንደሌለው ተረድተው አብረዎቸው እንዳይታዩ መፈለግ ይሆን ።

ሽልማትን በሚመለከት ከበርቴ አላሙዲ ከዚህ በፊትም በካፍ 50ኛ አመት የሽልማት ስነስርአት ላይ ባለመሸለማቸው እንዲሁ ለፌደረሽኑ የቅሬታ ደብዳቤ መፃፋቸውን ይታወሳል ይላል ሪፖርተር። ከዚህ ጋር ተያይዞ ነው የአሁኑን የፌደረሽኑን የይምሰል ምክንያት ላምነው ያልቻልኩት። ይበልጥም የጠቅላይ ሚኒስተሩ ቢሮ የፕሮቶኮል ሹሞች ከጠቅላይ ሚኒስተሩ ጎን የሚሸለሙትን ካዩ በኃላ የሰረዙት መሆናቸውን እንጂ የፌደረሽኑን ምክንያት ለመቀበል ያዳግተኛል።

ይህን ሳስበው ከበርቴው ሁሉንም የሚያደርጉት ለሽልማት ይመስልባቸዋል።አንድ ነገር ከበርቴውን ምክር ብባል የምነግራቸው ቢኖር ከኢትዮጵያ ህዝብ የዘላለም ሽልማት እንዲያገኙ ከፈለጉ ለእውነት ለሃቅ መቆም እንጂ በማመልከቻ የሚገኝ ሽልማት ምንም ጥቅም እንደሌለው ሊያውቁት ይገባል። በሚሰሩት ስራ ለመመሰገን ከፈለጉ የተሰጣቸውን ዘረኛ የሆነውን የንብ ካኒተራ መልሰው የኢትዮጵያን ባንዲራ ቢለብሱ ከዚህ በፊት ለኢትዮጵያ እንደተሰውት ኢትዮጵያውያን በታሪክ የክብር ቦታ ላይ ይፃፋሉ ። ከዚህም በየወቅቱ አልተሸለምኩም ከሚለው አስቂኝ ማመልከቻ ይድናሉ።

ስለኛ የሚያስብ በሰላም ይክረም
በልጅግ አሊ